# ውኃ አጣጭ ... ዳሰሳ

ከታምራት ኃይሌ

*... ለአዳም ግን ተስማሚና ረዳት ጓደኛ ገና አልተገኘለትም ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከባድ እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገ፤ አንቀላፍቶም ሳለ ከጐኑ አጥንቶች አንዱን ወሰደና ባዶውን ቦታ በሥጋ ሞላው ... የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጐ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት፡፡*

*አዳምም፤"እነሆ በመጨረሻ እኔኑ የምትመስል አገኘሁ ፤እርስዋ ከአጥንቴ የተገኘች አጥንት ናት፡፡ ከሥጋዬም የተገኘች ሥጋ ናት፡፡ ከወንድ የተገኘች ስለሆነች 'ሴት' ትባል" አለ፡፡ ወንድ አባትና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር የሚተባበረው ለዚህ ነው፤ ሁለቱም አንድ ይሆናሉ፡፡* (ዘፍጥረት 2:22-24)

*ልጄ ሆይ የአባትህን ትዕዛዝ ፈጽም፤ እናትህ ያስተማረችህንም ከቶ አትተው፤ የእነሱን መመሪያ ዘወትር ተከተል፤ቃላቸውን ዘወትር ጠብቅ ፤ የእነሱ ትምህርት በጉዞህ ይመራሃል፤በሌሊትም ጠብቅሃል፤... ከመጥፎ ሴቶች እንድትርቅና ከሌሎች ሰዎች ሚስቶች አሳሳች ቃል እንድትጠበቅ ያደርግሃል፡፡ ቁንጅናቸውን አትመኝ፤ በዐይናቸው ጥቅሻ አትማረክ፡፡ አንድ ወንድ ጋለሞታይቱን በአንድ እንጀራ ሊከራያት ይችላል፤ ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ማመንዘር ግን ያለውን ንብረት ሁሉ ያስጨርሰዋል፡፡ ልብስህ ሳይቃጠል እሳት በጉያህ ይዘህ መሄድ ትችላላህን? እግርህስ ሳይቃጠል የእሳት ፍም ረግጠህ መሄድ ትችላለህን ? ከሌላ ሰው ሚስት ጋር መተኛትም የዚህኑ ያህል አደገኛ ነው ፡፡ ይህን የሚያደርግ ሁሉ ከመቀጣት አያመልጥም፡፡ ሌባ በተራበ ጊዜ ምግብ ቢሰርቅ ለሰዎች አስገራሚ ነገር አይሆንም፡፡... የምንዝር ተግባር የሚፈጽም ሰው ግን ማስተዋል የጐደለው ነው፤ ሕይወቱንም በከንቱ ያጠፋል፡፡ ውርደትና ድብደባ ይደርስበታል፡፡ ሁልጊዜም እንደተዋረደ ይኖራል፡፡ (ሠረዝ የተጨመረ) መጽሐፈ ምሳሌ 6:20-34*

***"Who can find a virtuous wife? For her worth is far above rubies. The heart of her husband safely trusts her; so he will have no lack pf gain. She does him good and not evil all the days of her life." Proverb 31:10-12***

ነገርን በሰላምታ መጀመር ጥሩ ነው፤ ባህላዊም ሥርዓታዊም ነው፡፡ እንዲያው በድንገት ዘልሎ ቁም ነገር ውስጥ መግባት መልካም አይደለም፡፡ ነባር ይትበሃልን መጣስ አይገባም፡፡ እናም «ሰላም ለኩልክሙ» ብዬ መጀመርን ወድጃለሁ፡፡ በድጋሚ ሰላም ለሁላችሁም፡፡

በዛሬው ጽሑፌ ላወሳው የፈለግሁት ጉዳይ በጣም ሰፊና ማ በ ረ ኢኮኖሚያዊ ሚዛንም የሚደፋ ዐቢይ ጉዳይ መሆኑን ብዙዎቻችን የምንስማማ ይመስለኛል፡፡ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ በሁሉም ዓለማቀፋዊ ቅቡልነት ያላቸው ሃይማኖቶች ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥም ይህ የጋብቻ ጉዳይ በስፋትና በጥልቀት የተንቀራበጠ ስለመሆኑ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል፡፡

ለመሆኑ ጋብቻ ምንድን ነው? ከጥያቄዎች ሁሉ ከባዱ ይሄ ጥያቄ መሆን አለበት፡፡ ይህችን ጽሑፍ ልጫጭር ከመነሳቴ በፊት የጋብቻን ምንነትና ብያኔ ለመረዳት የተለያዩ ጽሑፎችን ለማገላበጥ ሞክሬያለሁ፤ በሃይማኖት ዙሪያና ከሃይማኖትም ውጪ፡፡ ጋብቻ ማለት "የሁለት ሰዎች የአብሮነት ሕይወት የትሥሥር ገመድ ነው" ከሚለው አደናጋሪ ብያኔ ጀምሮ ጋብቻ ማለት "በሁለት ተቃራኒ ጾታዎች የፍቅርና የመተሳሰብ ግንኙነት ላይ የሚመሠረትና በርካታ ቤተሰባዊ ኃላፊነቶችንም በጋራ ለመሸከም ቃል ገብተው የሚጣመሩበት ማኀበራዊ እሴት ነው፡፡" ብለው እስከሚያምኑት "ጤናማ" የሥነ ልቦና ምሁራን ድርሳናትና የሃይማኖት መጻሕፍት ድረስ ለመዳሰስ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ "እያንዳንዱ ሰው በራሱ ቢያንስ አንድ መጽሐፍ ይወጣዋል" ከሚለው ብሂል ብንነሳም እኔም ከዚህ ማኀበራዊ ሕይወት የተለየሁ ባለመሆኔ በራሴም ሆነ በሌሎች ላይ የደረሰውንና ሲደርስ የታዘብኩትን እንደየአስፈላጊነቱ ለማካተት ሞክሬያለሁ፡፡

ከተለያዩ ምንጮች እንደምንረዳው በተለይ በአሁኑ ዘመን ጋብቻ ሰፊ ትርጓሜና እንድምታ ካላቸው ማኀበረሰባዊ ዕድሜ ጠገብ ክንዋኔዎች አንዱና ምናልባትም ከመጀመሪያዎቹ ተርታ የሚካተት መሆኑ አይካድም፡፡ (የሰይጣን ጆሮ ይደፈንና) ዘመን አመጣሾቹን የወንድና ወንድ፣ የሴትና ሴት ወይም በሰውና በእንስሳት መካከል ይደረግ ጀምሯል የተባለውን ጋብቻ ከባህልና ሃይማኖት አንጻር ውጉዝ ከመኣሪምስ በመሆኑ ለጊዜው እንተወውና ገብስ ገብሱን ብቻ እንኳን እናውራ ብንል - በገብሱ ውስጥ ያለውን እንክርዳድ ጭምር ማለት ነው - የጋብቻን ስንክሳር ዝርዝረን አንዘልቀውም፡፡ ከስያሜው ብንነሳ ጋብቻ ስንል ይበልጥ የሚያተኩረው በእጮኝነትና በትዳር መካከል ያለውን ህጋዊ የትሥሥር ሂደት ወይም ሥርዓት መሆኑን ማጤን ይቻላል፡፡ ጋብቻ በሴትና በወንድ መካከል የሚመሠረት እንደ መጽሐፉ ቃል ወንዱም ሴቷም ቤተሰባቸውን ትተው እንደደጉ የጥንት ዘመን ቃለ መርዓዊ "አንድ አካል አንድ አምሳል" የሚሆኑበት ፤ከዚያም እነሱም በተራቸው በሞቀ ትዳር ውስጥ ልጆችን ተክተው ሀብትና ንብረት አፍርተውና በአንድ ሀገር ህልውና ላይም እንደ አንድ ጡብ የበኩላቸውን ታሪካዊ ድርሻ አበርክተው የሚያልፉበት ማኀበራዊ መዋቅር መሆኑን ለማጠየቅ ዋቢ መጥቀስ አያስፈልግም፡፡ በተባበሩት መንግሥ ት የ1948ዓ.ም .ዜ.አ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ አንቀጽ 16 መሠረት ጋብቻ ለአቅመ አዳምና ሔዋን በደረሱ ሴትና ወንድ ጥንዶች መካከል በፈቃዳቸው ተመሥርቶ ቤተሰብና ሀብት የሚያፈሩበት፤ዜግነት ፣ዘርና ሃይማኖት ሳይገድባቸው ትዳር የሚመሠርቱ ተጋቢዎች በመጋባት ወቅትም ሆነ ከጋብቻ በሁዋላና በፍቺ ጊዜ ኩል መብት ያላቸው፤የአንድ ሀገርና ብረተሰብ መሠረት ንደመሆናቸውም የመንግሥት ጥበቃና ከለላ ሊለየው የማይገባ አነስተኛው ማ በራዊ ተቋም ንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ማይክሮሶፍት ኢንካር ም በ2008 ዕ ትሙ ቀጥሎ የተመለከተውን አስፍሯል፡፡

Marriage is socially recognized and approved union between individuals, who commit to one another with the expectation of a stable and lasting intimate relationship. It begins with a ceremony known as a wedding, which formally unites the marriage partners. A marital relationship usually involves some

ወደ ገፅ 43 ዞሯል

# ውኃ አጣጭ …

ከገጽ 24 የቀጠለ

kind of contract, either written or specified by tradition, which defines the partners' rights and obligations to each other, to any children they may have, and to their relatives. In most contemporary industrialized societies, marriage is certified by the government.

In addition to being a personal relationship between two people, marriage is one of society's most important and basic institutions. Marriage and family serve as tools for ensuring social reproduction. Social reproduction includes providing food, clothing, and shelter for family members; raising and socializing children; and caring for the sick and elderly.

ዋናው የጋብቻ ምንነትና ማኀበራዊ ፋይዳ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ይምሰል ንጂ አፈጻጸሙ ግን ከሀገር ሀገርና ከማኀበረሰብ ማኀበረሰብ የሚለያይ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህም ሲባል ከመተጫጨት ሂደት ጀምሮ እስከ ጋብቻውና ምናልባትም ጋብቻው ያልሰመረ እንደሆነ እስከ ፍቺው ሥርዓት ድረስ በየሀገሩ እንደየሕዝቦች የባህልና የእምነት መለያየት በነዚህ በተጠቀሱት ጋብቻ ነክ ይትበሃሎች ላይም የጐሉ ልዩነቶች መኖራቸው የታመነ ነው፡፡

ለምሳሌ የሀገራችንን ሁኔታ ብናይ ከብሔር ብሔር ወይም ከብሔረሰብ ብሔረሰብ ይቅርና በአንድ ብሔር / ብሔረሰብ ውስጥ ሳይቀር በጣም የጐላም ባይባል መጠነኛ ልዩነቶች መኖራቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በጐንደር የሚታየው የአተጫጨትና የጋብቻ ሥርዓት በወሎ ከሚታየው አንድ ዓይነት ይሆናል ብለን አንገምትም፡፡ በወለጋ የሚታየው የአተጫጨትና የጋብቻ ሁኔታ በአርሲ ከሚታየው ጋርም እንዲሁ፡፡ በዚህ ስሌት ውስጥ ከሚገቡ ታሳቢ ቁም ነገሮች መካከል ማን ለማን ማንን ያጫል? የተጋቢዎች የዕድሜ መነሻ ገደብ ለሴት/ለወንድ ስንት ነው? ጥሎሽ ከማን ወደ ማን ? የወላጆች ሚና? … የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከውጭ ገራት መካከል የአሜሪካ ስቴቶችን የጋብቻ ህግ ለአብነት ያየን እንደሆነ በWorld Book of Encyclopedia መሠረት ሁሉም ግዛቶች ተመሳሳይ ደንብ የላቸውም፡፡ ዕድሜን በተመለከተ ብዙዎች ለሴትም ለወንድም 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸው ጋብቻ መመሥረት ሲችሉ ጥቂቶች (Nebraska and Wyoming ከ19 ዓመት በላይ፤ Mississippi and Rhode Island ከ21 ዓመት በላይ) ከሌሎች ይለያሉ፡፡ በሀገራችንም የቀድሞውን አያድርገውና ከቅርብ ዓመ ት ወዲህ የአብዛኛው ሕዝብ የህግ ዕውቀት እየዳበረ በመምጣቱና ያለ ዕድሜያቸው የሚዳሩ ሕጻናት ሴት ልጆችም ለአካለ መጠን ሳይደርሱ ለባል በመሰጠታቸው ምክንያት እየደረሰባቸው በነበረው አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ችግር ሳቢያ በተለይ በአሁኑ ወቅት ከ18 ዓመት በታች የመዳሩ ሁኔታ እየቀነሰ መምጣቱ ይነገራል፡፡

በባህላዊ፣ በሃይማኖታዊም ሆነ በዘመናዊ የማዘጋጃ ቤት ጋብቻ ሥርዓት መጋባትና ትዳርን መመሥረት ፣ የሦስቱን ጉልቻ ጉለታም ተከትሎ ከሚመጣው የፍቅርና የመተሳሰብ የሞቀ ትዳር ውስጥ ልጅን ወልዶ መሳም፣ በወግና በሥርዓት አሳድጐና አስተምሮ ለወግ ለማዕረግ ማብቃት የትዳር አጋሮችንና ቤተሰብን ብቻ ሳይሆን ሀገርንና ሕዝብን የሚጠቅም ቅዱስ ተግባር መሆኑ ፀሐይ የሞቀው እውነ ነው፡፡ የአንድ ጋብቻ መጽናትና ትዳሩ ወይም ጐጆው በሠርጉ ዕለት በሚዜዎችና በታዳሚዎች እንደተዘመረለት "የአብርሃምና የሣራ" ጋብቻ ሆኖ እስከዕድሜ ፍጻሜ መዝለቅ በሁሉም ዘንድ በጉጉት የሚጠበቅና ለጤናማ ማኀበረሰብ ግንባታ መሠረታዊ ግበኣት የሚሆን ባህላዊ ክንውን ነው፡፡ ከእጮኛነት ዘመን አንስቶ እስከጋብቻው ዕለት ድረስ ሁለቱን ተጋቢዎች በዋናነት አማክሎ ከቅርብ ቤተሰብና ጓደኛ እስከሠፈርተኛ ድረስ ሲያሳትፍ የነበረና በደመቀ ቃና ዘገሊላዊ የጋብቻ ሥርዓት የተቋጨ ጥምረት እንደመጻሕፍቱ ድንጋጌ "እግዚኣብሔር አንድ ያደረገውን ማን ሊለየው?" እንደተባለው ወይም በብሂላችን "ባልና ሚስት ከአንድ ምንጭ ይቀዳሉ፡፡" ተብሎ የሁለቱ አንድነት እንደተገለጸው ፍቅራዊ ቁርኝታቸው ሳይላላ፣ ቤተሰባዊ ውበታቸው ሳይደበዝዝና ማኀበረሰባዊ ቅቡልነታቸው ጥያቄ ውስጥ ሳይገባ ያረጁ ተጠቃሚው ይበዛል፤ ተጐጂው ይቀንሳል፡፡

እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ግን እንደመጥፎ ዕድል ሆኖ በተለይ በዚህ ዘመን ከምኞት በዘለለ የሠመረ ጋብቻና ትዳር ለማየት እምብዛም የታደልን አይመስልም፡፡ ይህን ስል ግን በብዙ ነገሮች ለሌሎች አብነት ሊሆኑ የሚችሉ ፤ ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ሁሉ የአሉቧልታን ውሽንፍራዊ ወላፈን በዋናነት ጨምሮ በበርካታ ማዕበሎች ተፈትነው በመቻቻልና በአስተዋይነት ትዳራቸውን በጽናት ያቆሙ እንዲያም ሲል ከመጠነኛና ከሚጠበቅ ዕለታዊ የሃሳብ ግጭት ውጭ ለክፉ በሚሰጥ አምባጓሮ ተዘፍቀው ትዳራቸውን በፈግጠው ፈግጪው ያልበተኑና በውጤቱም ልጆችን ለሥነ ልቦናዊ ምሥቅልቅል፣ እነሱን ለማኀበራዊ ትዝብትና ለአጠቃላይ የሕይወት ቀውስ ያልዳረጉ ጠንካሮች የሉም ማለቴ አይደለም፡፡ እነዚህን ዓይነት ጥቂት ጥንዶች ስናይ የምንደሰተውን ያህል የጋራ ቤታቸውን የነገር ተኩስ ሩም ው ለአፍ የማያባራበት የዘወትር ዐውደ ዉጊያ አድርገው በነጋ በጠባ የሚጨቃጨቁ፣ ለወለዱዋቸው የአብራካቸው ክፋዩች የአሁንና የወደፊት ሕይወት ሳይሆን ብል የሚበላውንና እሳት የሚያጋየውን ዓለማዊ ሀብትና ንብረት አምልከው በርሱ ምክንያት የአርማጌዶ ጦርነት ውስጥ የሚዘፈቁ፣ አብረው መኖር ካልቻሉ ተለያይተው (መለያየት ባይመከርም) በእህትና ወንድምነት ቀጣይ ሕይወታቸውን ከፈለጉት ሌላ ሰው ጋር (ካሻቸውም ብብህትውና) መምራት ያልቻሉ እጅግ ብዙ የትዳር ላይ አመጾኞችን ስንታዘብ ክፉኛ መተከዛችን አይቀርም፡፡ ከዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ጋር በተያያዘ እኚህ የፈረደባቸውን "ዘመን " እና "ሠይጣን" እጃቸው ሳይኖርበት የራሳችንን ባሕርይ መግራት አቅቶን የሚመጣብንን ጣጣ ሁሉ "ዘመኑ እኮ ነው!" ወይም "አጅሬ ሠይጣን ነው እንዲህ የሚያናቁረን…" እያልን አበሳውን ወደሌላ ወገን የምናላክክ ጥቂቶች አይደለንም፡፡

ዚህ ላይ ሁለት አስተማሪ ሊሆኑ የሚችሉ ምሳሌዎችን መጥቀስ ፈልጋለሁ- ከሰማሁትና ካነበብኩት፡፡ በአንድ ገዳም ውስጥ በኩዳዴ ፆም ሊያውም በዕለተ ዓርብ አንድ መነኩሴ ዕንቁላል መብላት ያምራቸውና ዕንቁላሉን በ ጃቸው ይዘው በጡዋፍ መብራት ያገላበጡ ሲያበስሉ የገዳሙ አበምኔት ይደርሱባቸውና « ንዴ! አባ ምን ነካዎት? በፆሙ ምድር

☞

ከገጽ 42 የቀጠለ



ዕንቁላል?...» ይሉዋቸዋል፡፡ ቀቅለው ወይም ጠብሰው ንዳይበሉ ሰው ይደርስባቸውና ንዳያዋርዳቸው ሰግተ ው በጡዋፍ ብርሃን ዕንቁላል ሲጠብሱ የነበሩት መነኩሴም የፈሩት በመድረሱ በድንጋጤ ርደው « አባቴ ይቅር ይበሉኝ- ሠይጣን አሳስቶኝ ነው» ይሉዋቸዋል፡፡ ይሄኔ አንድ ሠይጣን የመነኩሴውን ድርጊት ከመነሻው ጀምሮ በቅርብ ርቀት ሆኖ በአግራሞት ሲከ ተል ንደነበረ ይገልጽና በአምሳለ ሰብዕ ተከስቶ « አንት ዉሸ ም! ዕንቁላል በጡዋፍ ንደሚጠበስ ኔ ራሴ ገና ዛሬ ነው ከአንተ የተማርኩት - ለምን በኔ ሳብባለህ?» በማለት አዋ ረደው ይባላል፡፡ ስንቶቻችን የራሳችን ሥሪት የሆኑ ጢኣቶችንና ወንጀሎችን በፈረደበት ሠይጣን ወይም ሌላ አካል ንደምናላክክ ቤቶቻችን ይቁጠሩት፡፡

ሁለተኛው ይሄውና- ሁለት ባልና ሚስት ከራት በሁዋላ ጠብ ቢጤ ይጀምሩና በነገር ጅራፍ መሸነቋቆጥ ይይዛሉ፡፡ ይሄኔ ቤ ቸው ማቶት ላይ ሆነው የጠቡን መጋጋል በጉጉት ይጠባበቁ ከነበሩት ባልና ሚስት ሠይጣኖች መካከል ሚስትዮዋ « በል አሁን ንግባባቸውና ጠባቸውን አባብሰን ደም ናቃባቸው» ስትል ባልዮው ቀበል አድርጎ «አሁን ቆይ፤ ማን ጠራንና? ምን አስቸኮለሽ? ያደርስሽ የለም?» ይላ ል፡፡ የጥንዶቹ ጠብ ከመብረድ ይልቅ የገነነ ይሄድና ባልዬው « አንቺ ሴት፤ ተይ ባክሽን ሠይጣን አትጥሪብኝ!» ሲል ሳይጠሩ መግባ ቸውን ያከላክል የነበረው አባወራ ሠይጣን ለሚስቱ « በይ አሁን ተጋብዘናልና ገብተን ያፈተተንን ናድርግ» ይላ ል፡፡ ባልና ሚስቱ አጋንንት በባልና ሚስቱ ሰዎች አናት ዉስጥ ተቆናጥጠው የሠሩትን ሠሩ፡፡ የዚህ ብሂል መልዕክት ለችግሮቻችን መባባስ ተጠያቂዎቹ ይበልጡን ኛው መሆናችንንና መፍትሔውም ከኛው ንደማይርቅ የሚያስገነዝብ ጭብጥ አለው፡፡

ከመነሻው የትዳር ቀምበር ሲባል እጅግ ከባድ ሸክም መሆኑ ሳይ ለም የተ ፈ ነው፡፡ ተጋግዘው እኩል ካልተሸከሙት የቀምበሩ ክብደት ያጋደለበትን መቀናጆ ክፉኛ ሊደቁሰው ይችላል፡፡ የብዙ ትዳሮች ችግር ደግሞ "ይህን ቀምበር ከማን ጋር ብሸከመው ነው ሸክሙ ሳይሰማኝ እስከመጨረሻው በሰላምና በፍቅር የምዘልቀው? ... " ብሎ ቀድሞ ያለ ማገናዘብና በቂ ባልሆነ ሆይ ሆይታዊ የወረት ፍቅር ጋብቻን በጥድፊያ መመሥረት መሆኑን ለመረዳት ጥናት ማካሄድ አያስፈልግም፡፡ በመሠረቱ ከዘመን መለዋወጥ ጋር አብረው የሚከሰቱ ለመከሰታቸው መንስኤ ግን ሰው እራሱ እንጂ እንደቸረት በራሱ ፈለግ የሚተመው 'ጊዜ' እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበ ል፡፡

በሌላ ወገን ለመፍትሔያቸው የኛን ትኩረት የሚፈልጉ አንዳንድ ችግሮች ንዳሉ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል የሃይማኖት መላላት ወይም ከለመዱት የሃይማኖት ሥርዓት ያላንዳች የተሻለ አማራጭ ማፈንገጥና መውጣት፣ የሞራል መዝቀጥ፣ከባህል ማፈንገጥ፣ የኀሊና ሚዛን መዛባት፣ ተስፋ መቁረጥና ድህነት፣ ልጅ ያለመውለድ ወይም ቁጥራቸው ከአቅም በላይ የሆነ ልጆች መኖር፣ ከጋብቻ በፊት የነበረ ሕይወት የሚያሳድረው ተፅዕኖ፣ አቅምን አውቆ ለመኖር የሚያስችል ሞራላዊ ብቃትና ሃይማኖ ዊ ዕውቀትና ጥበብ መጥፋት ወዘተ. በትዳር ላይ የሚየሳድሩት አሉ ዊ ጫና ከባድ ነው፡፡ ነዚህ ማ በራዊ የአስተሳሰብና የአመለካከት ችግሮች በትዳር ላይ ብቻ ሳይሆን ሰው እንደሰውነት አካላዊና መንፈሳዊ ጤንነቱን ጠብቆ ከሌሎቸ እንስሳት በአፈጣጠር እንደተለየ ሁሉ በኑባሬም የራሱን ጠገግ ይዞ እንዳይዘልቅ የሚያሰናክሉ ዕንቅፋቶች ስለመሆናቸው ከተጨባጩ የዕለት ከዕለት ገጠመኞችን ተነስተን መመሥከር የምንችለው አሳዛኝ ዉነ ነው፡፡ እንደ አጠቃላይ እውነት ከሌሎች እንስሳት ይልቅ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ተፈጥሮኣዊ ጠባዩን - ሊያውም በጣም በቀላሉ - መለዋወጥ የሚችል ፍጡር ቢኖር ሰው ብቻ ነው፡፡ ምናልባት ማሰብና ማቀድ ፣ ያለፈን ከአሁንና የአሁንን ከወደፊት ጊዜ ጋር ማገናዘብ መቻሉ ከሌሎች እንስሳት ስለለዩት ይመስላል የሰው ልጅ ባሕርዩን እንደፈለገውና እንደየወቅቱ ሁኔታ መለዋወጥ ያስቻለው፡፡ በዚያ ላይ እውነትን ለመደበቅ የተፈጠረ እስኪመስልበት ድረስ እንዳሻው የሚጠቀምበትን ቋንቋ ንብረቱ ካደረገ ወዲህ ሳይሆን አይቀርም ከቀሪው የእንስሳት ዓለም በጉልህ የተለየው ቢባል ሳያስኬድ አይቀርም፡፡ ለምሳሌ ውሻን ብንወስድ ከተፈጥሮኣዊ የመውደድና የመጥላት ባሕርይው ዉጪ ማስመሰልን የሚያዉቅ አ ላይ ፍጡር መሆኑን ማስ ረዳት የሚችል ሰዉ ያለ አይመስለኝም ፡፡ ዉሻ ከታመነ ታመነ፡፡ መታመንንና መክዳትን እያፈራረቀ ማንንም ግራ አያጋባም፡፡ ሰው ግን እየሳቀ ያቀርባል ፤ አቅርቦም ያስለቅሳል፡፡ የወደደ መስሎ ይጠጋል ፤ ተጠግቶም የተቀበረ ጥላቻ ውን በአሳቻ ሥፍራና ጊዜ አውጥቶ ስከ ልፈተ ሕይዎት ሊደርስ የሚችል ጉዳት ያደርሳል፡፡

ወደ ዋናው ጉዳያችን እንግባ- «ንግባኢኬ ሃበ ጥንተ ነገር» ይለዋል ቅዳሴ ማርያም ዘግዕዝ ፡፡ የፍርድ ቤት ውሎዎችን ፣ የመንደር ሽምግልናዎችን ፣ በቤተ አምልኮቶች አጸድ ዙሪያ የሚካሄዱ የቤተ ዘመድ ጉባኤዎችን ... ብንመለከት እጅግ ብዙዎቹ የተጣላን ለማስማማት ወይም ደም የተቀባን ለማስታረቅ ሳይሆን የተናጋን ትዳር ለመጠገን ወይም እህል ውሀቸው ያለቀን ጥንዶች ለማፋታት ንደሆነ ቢ መን ከ ዉነት መራቅ አይሆንም፡፡ ይህ እንግዲህ ለይቶላቸው አደባባይ የወጡትንና ጉዳያቸው በባህላዊ ሽምግልና ወይም በዘመናዊ የፍርድ ሂደት የተያዘውን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን እኔም፣ አንቺም፣ አንተም፣ እርስዎም፣ እነኚያም ፣እነኚህም... በውሃ ቀጠነ ሰበብ ክፉና ደግ ባልለዩ ምቦቀቅላ ሕጻናት ፊት ሳይቀር ሰርክ አተካራ እየገጠምን የምንነዛነዝ ፣ ከኛ የተሻለ ሰላም ያላቸው ጐረቤቶቻችን ሳይቀሩ "እንግዲህ ጀመራቸው!" እስክንባል በዱላ ቀረሽ ንትርክና በሽመል ቁርቋሶ የምንጠመድና በዚያም ሰበብ ተፈነካክተን ፓሊስ ጣቢያና ሐኪም ቤት የምንመላለስ፣ አንዳችን የአንዳችንን ከቤት መውጣት ወይም ከአካባቢ ዘወር ወይም ከሀገር ገለል ማለት ጠብቀን ከእሥር እንደተፈታ ጥጃ በግልጥና በአደባባይ የምንፈነጭና ቀሚስ የለበሰችና ሱሪ ያጠለቀ ሁሉ አይቅረን የምንል ፤ «ከእርሱ/እርሱዋ ሌላ ላሣር» ብለን የገባነውን ቃል ኪዳን ገና ከጫጉላ ቤት ሳንወጣ የምናፈርስ ፤ ለርሱ/ለርሱዋ ያለቀስን መስለን በልባችን የምሥጢር ኋዳና በአዕምሯችን የስርጥ ዛ ለሰነቀርነው ሌላ ሰው የምናነባ፣ ይህን ሁሉ ቅጥፈት ግን - ዕድሜ ለሰውነታችን- ሰው መሆናችን ባጐናጸፈን ዋና የማጭበርበሪያ መሣሪያ ቋንቋ አማካይነት ግብዝነ ችንንና ዕኩይነታችንን ማር በተቀቡ መርዛማ ቃላት ጀቡነን መቀናጆኣችንን የምናታልል ... እጅግ ብዙዎች መሆናችንን ማንም ሳይነግረን እራሳችን እናውቀዋለን፡፡ በዚህም ያልተገባ ምግባራችን « ባክህን ው አጣጩን ስጠኝ» ያልን ስንነዘንዘው የነበረውኝ ፈጣሪን የምናሳዝን ብዙዎች ነን፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው እርስ በርስ የሚቃረኑ ሁለት ነገሮችን የሚወድ የዚች ምድር አባል ሰው ብቻ ነው፡፡ የጥላቻና የፍቅርን ካርዶች በአንድ ጊዜ ይዞ እንዳስፈላጊነታቸው የሚጠቀም ከሰው ሌላ ሌላ ፍጡር ስለመኖሩ ስካሁን የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ አንዳንዶቻችን በትዳር ውስጥ የሚገኙ ጥቂት ነገሮች ይስቡንና ትዳርን ☞

ከገጽ 42 የቀጠለ



ለይምሰልና ለ ይ ወይም ለሆነ ሥውር ዓላማ እንይዘዋለን፡፡ ከሠርጋችን ማግሥት ጀምሮ ግን ትዳር ቀምበር መሆኑን እንረሳና የቀምበሩን ሸክም ለአንደኛው ወገን ሰጥተን ንደዱሮው ንደላጤነት ጊዜያችን በአስረህ/ሽ ምቺው መፈንጠዝ ያምረንና ያን ንያያዘዋለን፡፡ ለፍንጠዛችንም የተለያዩ አመክንዮዎችን እንሰጣለን፡፡ "አልጋ ላይ አልተመቸኝም/ችኝም፤ ይጨቃጨቀኛል/ትጨቃጨቀኛለች፣ እንደበፊቱ ሊሆንልኝ /ልትሆንልኝ አልቻለም/ችም፤..." በሚሉና በሌሎችም ጥቃቅን ሰበቦች ድንገት ደርሰን የሁለት ዓለም ሰዎች የምንሆን ጥቂቶች አይደለንም፡፡ በስሜት ፈረስ ሽምጥ ስንጋልብ ለጊዜው የሚ የን የኛ መደሰት ንጂ የልጆች ሕይወት መናጋትና የትዳራችን ክር ሰልስሎ ሊበጠስ መቃረብ አይደለም፡፡ አንዳንዶቻችን የቤቱም አይቀረንም፤ የውጭውም አይቀረንም- « ያውጡብ ምቢ-ያግቡብሽ ምቢ» ንዲሉ ንሆንና ለያዥ ለገራዥ ያስቸገርን የሰዎችን ሕይወት በሰቆቃ ንሞላለን፡፡ ይሁንና ሁለት ወዶ እስከዘለቄታው መቆየት የማይቻል በመሆኑ ቆይቶ ቁርጡ መለየቱና አንዱን ንድንመርጥ መገደዳችን የማይቀር መሆኑን ጊዜ ባለዉሉ ቅጬን ሲነግረን አመሻሽ ላይ መደናበር ንጀምራለን፡፡ በዚያን ጊዜ ተጐጂው በሁለት ቢላዎ ሲበላ የነበረው መቀናጆ ብቻ ሳይሆን ሁሉምና በተለይ ደግሞ በትዳሩ ውስጥ ልጆች ተፈጥረው ከሆነ በዋናነት እነሱ ናቸው ናት አባት ባፈነዱት ሳተ ገሞራ ሳቢያ ምድር ወደ ሲዖልነት ተለውጣባቸው ካለ ጢያ ቸው ያልበሉትን ዕዳ ሊከፍሉ የሚገደዱት፡፡ ይህ ደግሞ በቀላሉ ያሳዝናል ተብሎ በቻ የሚ ለፍ አይደለም- ኩነኔም ጭምር ነው- በዚህ ድርጊት መኮነን ካለ፡፡

«ቦሃ ላይ ቆረቆር» ንዲሉ የትዳሩን መንሻፈፍ ተገን አድርጎ ያ መናጢ ተውሳክ በተጋቢዎቹ መሃል ሰርስሮ ገብቶ ከሆነ ደግሞ የቤቱ መንኮ ኮት በ ንዴት ያለ ፍጥነት ሊቀለጣጠፍ ንደሚችል የሚያውቅ ያውቀዋል፡፡ «ውሃ ሲወስድ ያሳሳቀ ነው» ንዲሉ ብዙዎች ሞኞች የዚህን ዓይነቱን አስቀያሚ የመጨረሻ ዕጣ ከወዲሁ በቅጡ ሳያስተውሉ የቀሩ አይወድቁ አወዳደቅ ሲወድቁ ማየት በተለይ በአሁኑ ዘመን ያልተለመደ አይደለም፡፡

ለብዙ ትዳሮች መፍረስ እንደምክንያት የሚጠቀሱ በርካታ ነጥቦች አሉ፡፡ ጥሩ ትዳር የሚመሠርቱ እነማን ናቸው? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ አንዱ 'ሊቀ ሊቃውንት' ሲመልስ "ዓይነ ሥውር ሚስትና መስማት የማይችል ባል" ያለውን አንርሳና ትልቁ የትዳር ጸር አሉቧልታና

ወሬ መሆኑን መዘንጋት አይኖርብንም፡፡ የወሬው ሀሰት ውነትነት እንዳለ ሆኖ አንድን ትዳር ለማፍረስ ብዙ ወጭ ከማያስወጡ ነገሮች መካከል አንድን ወሬ ፈጥሮም ቢሆን ማናፈስና ዒላማውን አነጣጥሮ ግቡን እንዲመታ ማድረግ የነበረና ያለ ሕይዎ ችን በዚህ መልክ መቀጠሉ የማያመልጡት ሰው የመሆን ዕዳ ከሆነም ወደፊትም የማይቀርልን ማ በራዊ ጠንቅ ነው፡፡ ዉነ ው ይሄ ከሆነ ዘንድ አንድ ወሬ ሲናፈስ በችኮላ በሚወሰድ እርምጃ የማይመወጡት ችግሮና ጸጸት ውስጥ ከመግባት አስቀድሞ መጠንቀቅ ተገቢ መሆኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡ ወሬው ከየት አቅጣጫ እንደተሰነዘረ ማጤን ፣ ለምን ዓላማ እንደተሰራጨ ማወቅ፣ እውነት ወይም ሀሰት መሆኑን ከገለልተኛ አካል ማጣራትና (የዜና ትን ኔ አስመሰልኩት ልበል?) በተረጋጋ ሁኔታ ከትዳር አጋር ጋር ተወያይቶ በጨዋ ደንብ ጨዋ ውሳኔ ማሳለፍ ከጨዋ ተጋቢዎች የሚጠበቅ ነው፡፡ ምንም ንኩዋን ብሂሉ « ቀድሞ ነበር ንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ» ያለ የተሠራን ስህተት ንዳናርም ቢገዳደርም «ከመሞት መሰንበት» የሚለውን ተለዋጭ ብሂል በማስ ወስ በተለመደ አገላለጽ ለማስረገጥ ያህል-**ላለመስማማት መስማማትም** ንዳለ መረዳት ከብዙ ያልተጠበቀ ችግር ያድናል፡፡

የኢኮኖሚ ችግር አንዱና ሌላው የሁከት መንስኤ ንደሆነ ይ መናል፡፡ ይህም ቢሆን ፍቅር እስካለ ድረስ በሥልጡን የውይይት መንገድ መፍትሔ መሻት ተገቢ ነው - ችግሩ ተካርሮ ትዳሩ ላይ አሉታዊ ጥላ ከማጥላቱ በፊት፡፡ ፍቅርና መተሳሰብ ካለ የገንዘብና የሀብት ጉዳይ የጠብ መንስዔ ሊሆን አይችልም፤ አይገባምም፡፡ የሀብት ይዞ ቸውን ቀድመዉ የሚያውቁ ባልና ሚስት ትዳራቸውን ከጀመሩ በሁዋላ ምን አዲስ ገንዘብ ነክ ነገር ሊያጣላቸው ይችላል? በርትቶ በመሥራት ችግርን ማስወገድ የተቻለስ የምን መወራከብ ነው?

የብዙዎችን ናላ የሚያዞረው ሌላው የትዳር ጠንቅ፣ ከትዳር ምሰሶዎች አንዱ የሆነው ፆታዊ ጨዋታ መሆኑ ከባህልና ከሃይማኖት ፈንጠር የሚለውን የሥነ ልቦና ምሁር ሲግመንድ ፍሩድን ጨምሮ "በሴት አካል ወንድ ያዛል፤ በወንድ አካል ሴት ታዛለች" እስከሚለው መጽሐፍ ቅዱስ ምክራቸውን የሰነዘሩበት ጉዳይ ነው፡፡ "የማይጨረስ ማኀበር በጠጅ ይጀመራል" እንደተባለው እንዳይሆንና ቀድሞ ፍ እፍ የተባለለት ትዳር ቆይቶ «ዓይንህ/ሽ ላፈር» መባባልና ወደ ውጭም መቀላወጥ እንዳይከተል ዚህም ላይ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድ ረግ ትዳርን ከመበ ተን አደጋ ይሠውራል፡፡ መተፋፈርን አስወግዶ በግልጽ የተነጋገሩ «ረሃብ ጥማትን» ቤት ባፈራው ማስ ገስ የተቻለ « የተ ቀደሰውን ለውሾች መስጠት»ና በውጤቱም ጎጆን ማናጋት ከብልህ አባወራ/ ማወራ አይጠበቅም፡፡ መተንፈስ የጀመረ ጕማ በፍጥነት ካልደረሱለት ለከፍተኛ ኪሣራ እንደሚዳርግ ሁሉ መንገጫገጭ የጀመረ ትዳርም በአፋጣኝ የችግሩን መንስዔ አጢኖ በግልጽ ውይይትና መግባባት ዕልባት ካላበጁለት ጦስ ጥምቡሱ ከባድ ነው፡፡ እርግጥ ነው በሀገራችን የጋብቻ መማክርት አለመኖራቸው (ካሉም አላውቅም ይቅርታ) በተወሰነ ደረጃ እየጐዳን ነው፡፡ ከትላልቅ ሰዎችና ከሃይማኖት አባቶች ምክርና ተግሳጽ ውጭ የረባ የጋብቻ ሥነ ልቦናዊ የምክር አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ያለን አይመስለኝም፡፡ ስለዚህ በቀላል ህክምና ከወዲሁ ሊፈወሱ ይችሉ የነበሩ የትዳር ቀውሶች እየተባባሱ ሄደው ለፍቺ እንዲያም ሲል ቁጥራቸው በቀላሉ የማይገመት ጥንዶችን ለኅልፈተ ሕይወት እየዳረጉ ይገኛሉ፡፡ አንድ ወቅት ሠፈሩን ያስቀና ትዳር- እንዳይሆን ሆኖ ሲቀርና ልጆች ለጐዳና አስቀያሚ ሕይወት፤ ተጋቢ ጥንዶች ለእሥራትና ለሞት ሲጋለጡ ማየት የሚዘገንን ግን ሊያመልጡት ያልተቻለ ማኅበራዊ ነቀርሣ ንደሆነ አለ ፡፡

ከተጋቡ በሁዋላ ፍቅርን ባግባብ ካለመያዝ የተነሳ የሚፈጠር መሰለቻቸት አንዱ የትዳር ጠንቅ ነው ፡፡ « ማን ያርዳ የቀበረ፤ ማን ይናገር የነበረ» ንዲሉ ረዘም ላሉ ዓመ ት በትዳር ላይ የቆየን ሰዎች ስለዚህም ሆነ ስለሌሎቹ ፀረ ትዳር አረሞች በተለይ ለአዲስ ተጋቢዎች ሊጠቅም የሚችል ተሞክሮኣዊ ምክር ቢጤ አናጣም ፡፡ ፈረንጆቹ «Familiarity breeds contempt.» ኛም አበሻዎቹ

«አብሮ አደግህ ጋር አትሰደድ» ወይም

«አወቅሁሽ ናቅሁሽ» የምንላቸው አባባሎች ችላ ተብለው የሚ ለፉ አይደሉም፡፡ በጥበብና በዘዴ ካልተያዘ ብዙ የመላመድና ብዙ የመተዋወቅ ጉዳይ ንኩዋንስ ነጋ ጠባና ከዓመት ስከ ዓመት አብረው በሚኖሩ የአንድ ማዕድ ተቋዳሾች ይቅርና አልፎ አልፎ በሚገናኙ ጓደኛሞች መካከል ንኩዋን ይሄ በጣም የመቀራረብ ነገር መናናቅን ሲፈጥርና ሰዎችን ወዳልተፈለገ የቅራኔ

አቅጣጫ ሲመራ ይ ያል:: በዚህ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው አስቸጋሪ ሂደት ዉስጥ የትምህርት፣የዕድሜ፣ የልምድና የዕውቀት መበላለጥ፣የአስተ ሳሰብና አመለካከት ልዩነት ፣ የገቢ መለያየት፣የቤተሰብ ዳራ(background) ፣ የባሕርይ አለመጣጣም፣ የሱሶች መከሰት ወዘተ. ያላቸው አሉ ዊ ተ ፅዕኖ ቀላል አይደለም። አንድ የንሥሐ ልጅ ለንሥሐ አባቱ ለቀሲስ መንበሩ ደስ ፤«መምሩ፣ ባክዎ ሚስት ያፋልጉኝ?» ብሎ ይጠይቃቸዋል:: « ንዴት ያለች ሚስት ልጄ?» ይሉ ል:: ሱም«ክብሩዋን የጠበቀች ጨዋ ልጃገረድ፣መልኩዋ የቀይ ዳማ፣ቁመትዋ ረዘም ብሎ አጠር ያለ፣ ሰውነትዋ ቀጠን ብሎ ወፈር ያለ፣ አፍንጫዋ ስልክክ ብሎ ዓይኖችዋ የብር አሎሎ የመሰሉ፣ በዕድሜዋ ለግላጋ ወጣት የሆነች፣ጠባይዋ ንጀራ የሆነና ቢረግጡዋት የማይከፋት፣ በትምህርትዋ የገፋች፣ጥሩ የወር ገቢ ወይም መተ ዳደሪያ ያላት፣ከሀብ ም ቤተሰብ የምትወለድ...(ዝርዝሩ አላለቀም)» ብሎ ይመልስላቸዋል:: በድማሜ ሲያዳምጡት የነበሩት ቄስ መንበሩ ጊዜ ሳያባክኑ « ንደዚች ያለች ምሉዕ በኩልሄ ሴት ከተገኘችስ አደራህን ለኔም ፈልግልኝ ልጄ! ቅስናዬን አፍርሼ ወዲያዉኑ አገባ ለሁ።» ነበር ያሉት:: ይህንን ቀልድ አዘል ሪክ ናንተም ውቁ ላችሁ፤ ኔም በቦ ው ስለነበርኩ ሰምቼዋለሁ- በጆሮየ በ ምቡሩ:(ቂ ቂ ቂ) ቁም ነገሩ ግን አንድ ሰው ራሱ ንኩዋን ጡዋትና ከሰዓት፣ጠጥቶና ሳይጠጣ... የተለያዩና ርስ በርስ የሚላተም ባሕርይ ባለቤት የሆነ በብዛት በሚስተዋልበት በዛሬው ዘመን ንዴት ወብስጭት ሌላን ሰው ንደኛ ይሁን ብሎ ስትንፋሱን ሳይቀር ለመቆጣጠር መሞከር ሞኝነት ብቻ ሳይሆን ዕብደትም ጭምር ነው:: ስለዚህ ሁለቱ ተጋቢዎች ከስሜት አምባላይ ፈ ረስ ወርደው የልዩነቶች መኖርንም አምነው መሰለቻቸትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ያለመደማመጥ ውጤት የሆኑ አለመግባባቶችንሳይገርሩ ንጭጭነ ቸው መቅረፍ ይኖርባቸዋል። ከሁሉም በላይ «ከአፍ ከወጣ አፋፍ ነው» ንደሚባለው መቅኒ ድረስ ሰርስሮ የሚገባና ስሜትን ስከወዲያኛው የሚያጎሽ መጥፎ ስድብ ወይ ዘለፋ ከመናገር መቆጠብ ተገቢ ነው ። ሲጣሉ መ ረቅ ንዳለ ፣ ሲፋቀሩም መጣላት ንዳለ አለመዘንጋት ብልህነት ነው:: ብዙ ከመናገር ይልቅ ብዙ ማዳመጥን መልመድ ከሰው ጋር ንደሚያኖር መገንዘብ ደግሞ ከፍተኛ ጥቅም አለው::

በባልዋ ሞገደኛነት ሳቢያ ለ25 ዓመ ት ትዳርዋ ሲበጠበጥ ቆይቶ በመጨረሻ ግን ጸሎትዋን ግዚኣብሔር ሰምቶ ትዳሩን ከመበተን ንዳዳነላት «The Power of a Praying Wife» በሚለው መጽሐፍዋ ልምዱዋን የም ካፍለን ወይዘሮ ኦማርሺያን የተ ባለች ሴት ንዲህ ትላለች፤«You can submit to God in prayer whatever controls. your husband– alcoholism, workaholism, laziness, depression, abusiveness, anxiety, fear, or failure- and pray for him to be released from it. … » 'የውጭ አልጋ የቤት ቀጋ' የነበረው ባል ተጸጽቶ ተመልሶኣል:: «It has been 25 wonderful years for me and 25 miserable years for her. » አለ- ከመልስ በሁዋላ:: ንግግሩን ወደ ሸር ንዳናዞርበት አደራ- ለማለት የፈለገው « ኔ ንደልቤ ስዘል ባለቤቴን ጎድቻ ለሁ» ነው:: ከዚህ ይሰውርን::

ሌላውና ትልቁ የትዳር ጠንቅ ቅናት ነው:: ቅናት የአንድ ሰው ሰብዓዊና ግላዊ ነጻነት ስከምን ድረስ ንደሆነ ንኩዋን መለየት የማያስችል ፍጹም የለየለት ደምባራ ንደሆነ ከብዙ ዎች ተሞክሮ መረዳት ይቻላል:: በቅናት ብዙ ትዳር ፈርሶኣል፤ብዙ ሕይወትም ጠፍቶኣል:: የቅናትን አባዜ በሚመለከት አንድ የቅርብ ጊዜ ምሳሌ ልስጥ፤ሂልተን ሆቴል ውስጥ ነው፤ለአንድ የቲቪ ቶክ ሾው ዝግጅት ቀረጻ ከ ደምን ሰዎች መካከል አንዱና ከሁኔ ው በጣም ሀብ ም የሚመስል ወፈራም ሰውዬ አጠገቤ ተቀምጦኣል::

ኔ ጨዋ ስለምወድ በዙሪ ያየ ካሉት ሰዎች ጋር ማውካካት ይዤያለሁ:: ሰውዬውን ሳጤነው ተ ጨንቋል፤ተጠቡዋል:: በቀዝቃዛው የማለዳ ወቅት ግንባሩ ላይ ችፍ የሚለውን ላብ አሥሬ በመሃረቡ ይጠርጋል:: ቦ ም ለመቀየር ፈልጌል፤ጨዋ ውና ይሉኝ ው ይዞት ንጂ:: ከዚያ በለሆሳስ ምን ንደገጠመው ጠየቅሁት- መልሱ ግን አስደነገጠኝ:: ናንተም ደንግጡ-« ሚስቴ በጣም ቀናተኛ ናት፤ ይህ ፕሮግራም በቲቪ ሲተላለፍ አጠገቤ የተ ቀመጠችውን ሴት ብ ይ ትገድለኛ ለች:: በቲቪም ይሁን በፎቶ ባጋጣሚ በካሜራ ውስጥ ገብ አጠገቤ ሴት ከ የች ቤት መግቢያ የለኝም::

'ቅምጥህ ናት? የወለደችልህ ናት?' ያለች ቁም ስቅሌን ነው የም ሳየኝ...» አለና የዚያን ሁሉ ስቃዩን መንስዔ ነገ ረኝ፤ ከዚያን ዕለት በፊት ለማንም አዝ ኜ ባላወቅሁበት ሁኔ አዘንኩለት፤ ከቁም ሥር ንዲወጣም ተመኘ ሁለት:: ንደዚህ ዓይነት የቅናት ልክፍቶች በሴትም በወንድም አሉ:: አንዳንዱ ሚስቴን/ባሌን አዩብኝ ብሎ/ላ ቡራ ከረዩ የሚል/የምትል አለ/ች:: የቅናት ዓይነቱና መዘዙ ብዙ ነው:: ቅናት ያፈረሰውን ቤት ቆጥሮ መዝለቅ አይቻልም:: አንዳንዴ ንዲያውም ምንም ባልተፈጠረበት ሁኔ ሲቀና « ከ ማሁ አይቀር ያንቺ/ያንተ መባሌ...» በሚል አላስፈላጊ ልህ ተነሳስተው ትዳርን ማመነቃቀር ብቻ ሳይሆን ከተጠ ረጠሩበት ሰው ጋር አንሶላ የሚጋፈፉ አልፎ ተርፎም አዲስ ጎጆ የሚቀልሱ የቅናት መዘዝ ሰለባዎች አሉ:: ስለዚህ ከዚህ ሞገደኛ ማ በራዊ ነቀርሳም ጠንቀቅ ማለቱ ከብዙ ውጣ ውረድ ያድናል::

«ቤ ቸውን ከፍተው ሰው ሌባ ይላሉ» ይላል ዘመነኛ አራዳ:: ይህን ያስ ወስኩበት ምክንያት ከልክ ባለፈ የራስ መተማመን « ኔ ንዲህ ያለ ነገር ሲያልፍም አይነካኝ፤ ከራሴ ሚስት/ባል ሌላ ቢጠበስም አይሸተ ኝም፤የኔ ባል/ሚስት ንዲህ ያለ ነገር አይነካካውም/ትም ...» በሚል ከንቱ ተ መጻድቆ ከተቃራኒ ፆ ጋር አሳቻ ቦ መገናኘት ወይም ለፈተና በሚጋብዝ መቼት ውስጥ መገኘት አደገኛና አላስፈላጊ መሆኑን መረዳት ከሠይጣናዊ የስሜት ፈረስ ሽምጥ ግልቢያ በሁዋላ ከሚመጣ ቁጭትና ጸጸት ይ ደጋል:: ናትዬ ሲጠበስ የማይሸት ነገር የለምና ጠንቀቅ ማለት ነው ደጉ:: በአንድ የስሜት ጡዘት ውስጥ ሆነን የምናደርገው ነገር ከዚያ ስሜት ስንወጣ የሕይወት ምህዋራችንን ወዳልተጠበቀ አቅጣጫ ስከመቀየር የሚያደርስ አስደንጋጭ ክስተት ሊፈጥርብን ስለሚችል ማንኛውንም ንቅስቃሴ ያችንን በንቃትና በአስተውሎት ልናራምድ ይገባናል:: ቁሶቹ « የምንላቸሁን ፈጽሙ ንጂ የምናደርገውን አትከተሉ» የሚሉትን ዚህ ላይ ባስ ውስ ቅር የሚሰኝብኝ አንባቢ ንደማይኖር ተስፋ አደርጋለሁ:: ለነገሩ ምንትስ ያለበት ምን አይችልም ንዳይሆንብኝ ንጂ የሚጽፍ ሁሉ የሚጽፈውን ሆኖ መገኘ ት አለበት የሚል የጅኔሻ ስምምነትም ሆነ ማግና ካር ዊ ሕገ ደንብ ስለሌለ ምን አስጨነቀኝ? ለማንኛውም ቸር ያሰንብተን- ነገርን ባጭር ካልቋጩት አንዱ አንዱን ዬወለደ ውለን ማደራችን ነው:: ስለዚህ ከአንድ ድረ- ገጽ ባገኘሁዋት ነገረ-ጋብቻ ብንሰነባበትስ?

***Marriage** - Today is a real "hit and miss" affair. People marry for all the wrong reasons and once married; they quickly realize, it's not what they thought it would be. Marriage should be considered nothing but a "long term" adventure; all about learning to "give and take", learning how to "compromise" along the way.*

*Sadly; couples are often too quick to divorce which makes them frustrated, bitter and sometimes twisted. If children are involved in a divorce, parents forget the devastating affects that can have on young minds trying to grow up and understand the complexities of life. Many children then just grow up emulating*

ወደ ገጽ 57 ዞሯል